

ተአምረኛው የደብረ ኃይል ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ
መምሪያ ተዘጋጀ

ላዩ አትጭ



ብእግዚአብሔር ፊት የምቆመው እኔ ገብርኤል ነኝ

www.ethiopianorthodox.org

ልዩ እትም



ከእግዚአብሔር ፊት የምቆመው እኔ ገብርኤል ነኝ

# ሊቃነ መላእክትና ነገደ መላእክት

መላእክት በሥነ ፍጥረት መጀመሪያ (በዕለተ እሑድ) የተፈጠሩ ረቂቃን ፥ መንፈሳውያን ኃይሎች ናቸው ። በሥጋውያን ፍጥረታት ጠባይ መብላት መጠጣት ፥ መልበስ ማጌጥ ፥ መድከም ማንቀላፋት ስለኑሮ ውጣ ውረድ ማሰብ መጨነቅ የሌለባቸው ንጹሐን ፥ ቅዱሳን ትጉኃን በመሆናቸው በባሕርዩ ንጹሕ ቅዱስ የሆነውን አምላክ ሲቀድሱ ሲያ መሰግኑ የሚኖሩ ስለሆነ ቅዱሳን ናቸው ።

የነገረ መለኮት ሊቃውንት አበው መንፈሳውያን የቅዱሳን መላእ ክት ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ እንደሆነ አመልክተዋል ። «መላእክቱን መንፈስ ፥ የሚያገለግሉትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው» ተብሎ በነቢዩ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ ነው ። ይህንም ለማለት ያስቻ ለው አገልግሎታቸውንና ተልእኮአቸውን በመመልከት ነው ። በእሳትና በነፋስ ይመሰላሉ እሳትና ነፋስ ኃያላን ፥ ረቂቃን ፥ ፈጣኖች ፈጻምያነ ፈቃድ ናቸው ። መላእክትም በፈጣሪና በሥነ ፍጥረት መካከል ለሚያከ ናውኑት አገልግሎት ኃያላን ፥ ረቂቃን ፈጣኖችና ፈጻምያነ ፈቃድ ስለ ሆኑ ከእሳትና ከነፋስ የተፈጠሩ መሆናቸው ተጽፎአል ። (መዝሙር ፩፻፫፡፬

በባሕርያቸው ማርጀት ማፍጀት ድካም ሕማም ሕልፈት ውላጤ የሌለባቸው ረቂቃን ኃያላን ስለሆኑ ሰማያውያን ፍጥረታት (መላእክት) የሚአስረዱ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙዎች ናቸው ። በተለይ አክሲማሮስ የተባለው ታላቅ መጽሐፍ ስለ ቅዱሳን መላእክት አለቆችና ነገዶች እን ዲሁም ስለተልእኮአቸው በሰፊው ይገልጻል ።

ወአመ ጸውዖሙ እግዚአብሔር ለመላእክቲሁ የአርጉ ላዕለ እስከ አርያም ወይወርዱ ታሕተ እስከ በርባሮስ ጽልመት እግዚአብሔር አምላክ መላእክቱን ለተልእኮ በጠራቸው ጊዜ ከላይ እስከ አርያም ከታች እስከ በርባሮስ ጽልመት ከዐይን ጥቅሻ በአነሰች ጊዜ ይወጣሉ ይወርዳሉ ከዚ ያም ተመልሰው ሕማምና ሞት ዕረፍትና ድካም በሌለበት አኗኗራቸው ሁነው ጌትነት የባሕርዩ የሆነውን እግዚአብሔር አምላካቸውን ሲያመ ሰግኑ ይኖራሉ ይላል ።

የግል ቤተ መጻሕፍት

www.ethiopianorthodox.org

እነዚህ በሰማይ ያሉ ሠራዊተ መላእክት (ሰማያውያን ፍጥረታት) በአሥር በአሥር ነገድ በሰባት ሊቃነ መላእክት (አለቆች) እንደሚመደቡ በዚሁ በአክሲማሮሱ መጽሐፍ ተገልጾአል ። አመዳደባቸውም ፤ እንዲህ ነው ፤

፩ኛ ቅዱስ ሚካኤል ኃይላት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ ።
፪ኛ ቅዱስ ገብርኤል አርባብ በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ ።
፫ኛ ቅዱስ ሩፋኤል መናብርት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ ።
፬ኛ ቅዱስ ሱርያል ሥልጣናት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ ።
፭ኛ ቅዱስ ሰዳክኤል መኳንንት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ ።
፮ኛ ቅዱስ ሰላትያል ሊቃናት በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ ።
፯ኛ ቅዱስ አናንኤል መላእክት (አጋዕዝት) በተባሉ ሠራዊት ላይ የተሾመ ። እያንዳንዳቸው ሰባቱ ሊቃነ መላእክት በዐሥር በዐሥር ነገድ የተሾሙ ሲሆኑ የሱራፌልንና የኪሩቢልን ነገድ ጨምሮ ሲቆጠር ግንዘጠና ዘጠኝ ነገድ እንደሚሆኑ መጽሐፈ አክሲማሮስ በሚገባ አድርጎ ያስረዳል ።

ቀድሞ ሳጥናኤል ከመሳቱ በፊት መቶ ነገደ መላእክት ነበሩ በኋላ ግን ሳጥናኤል ፈጣሪውን ክዶ ከክብሩ ተዋርዶ ከሠራዊቱ ጋር ምድረ ፋይድ ሲወርድ ዘጠና ዘጠኝ ነገድ ሁነዋል «ወሶበ ኢያእኮትኮ ለዘፈጠረከ እምነፋስ ወእሳት ፈጠረ ህየንቴከ ሰብአ ዘማሬ እማይ ወእመሬት እምነፋስ ወእሳት ከእሳትና ከነፋስ የፈጠረህን ባላመሰገንከው ጊዜ ከእሳትና ከነፋስ ከውኃና ከመሬት አመስጋኝ ሰውን ፈጠረ» ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን (የሰውን ልጅ) ከፈጠረው በኋላ በሳጥናኤል ምትክ መቶኛ ነገድ አድርጎ በክብር አስቀምጦታል ። ከማኅበረ መላእክት አስገብቶታል ።

## ኪሩቤል

ታላቁን የእግዚአብሔር ዙፋን የሚሸከሙ ሊቃነ መላእክት አርባዕቱ እንስሳ በመባል የሚጠሩ ገጸ ሰብእ ገጸ አንበሳ ገጸ ላህም ገጸ ንሥር የሆኑ ኪሩቤል አሉ በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ.፩ ከቍ ፬ እስከ መጨረሻው ባለው ስለ እነሱ ተገልጧል ። «ወምሉአን እሙንቱ አዕይንተ እምቅድም እስከ ድኅር (ራእ-፬፥፮-፰) በፊትና በኋላ ዐይኖች የተሞሉባቸው አራት እንስሶች አሉ እነዚህም ፍጡራን እንደሥራ ግምጃ ወይም እንደ ነብር ለምድ መላ አካላቸው የተዥጎረጎረ (በዐይን የተሞላ) እንደመስተዋት ስድ የሆነ አካል አላቸው» ኪሩቤል በአክሲማሮስ አመዳደብ ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት አንዱ ነገድ ናቸው መታሰቢያ በዓላቸው በየዓመቱ ኅዳር ፰ ቀን ይከበራል ።



## ሃያ ዓራቱ ካህናተ ሰማይ

አርባዕቱ እንስሳ ኪሩቤል የሚሸከሙትን ታላቁን የእግዚአብሔር ዙፋን ከበው የሚያጥኑ ናቸው ። «ወሰገዱ ቅድሜሁ ለዝክቱ ዘይነብር ዲበ መንበር እልክቱ እሥራ ወአርባዕቱ ሊቃናት ለዝክቱ ዘሕያው ለዓለመ ዓለም ፡ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃል ስለ ፈቃድህም ሁነዋል ተፈጥረውማል ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል» እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ (ራእ ፬ - ፱—፲፩) ።

በበጉ ፊት ወድቀው እያንዳንዳቸውም በበገና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ (ራዕ ፰ - ፩ ፡ ፯—፲፬) በማለት ወንጌላዊው ዮሐንስ የመሰከረላቸውና በራእዩ ያያቸው የጌታን መንበር የሚያጥኑ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ መታሰቢያ በዐላቸው በኅዳር ፳፬ ቀን ይከበራል ።

እነዚህ ሊቃነ መላእክት ዘወትር በታላቁ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ የማይለዩ ለሰዎች ምሕረትና ይቅርታ የሚለምኑ ናቸው ዕረፍቶሙ አኮቴቶሙ ምስጋናቸው ዕረፍታቸው ነው እንደተባለው ያለ ዕረፍት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ኪሩቤል በተሸከሙት መንበር ዙሪያ ሁነው ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ለዘለዓለም የሚኖሩ ናቸው ።

በሊቃነ መላእክት ተራዳኢነት
እግዚአብሔር አምላካችን ይጠብቀን አሜን ።

## አገልግሎት

የቅዱሳን መላእክት ዋናው አገልግሎት ፈጣሪያቸውን ያለዕረፍት ማመስገን ነው ። ሥጋው ያን ፍጥረታት ያለምግብና መጠጥ ሊኖሩ እንደማይችሉ ሁሉ ቅዱሳን መላእክትም ከእግዚአብሔር ምስጋና ተለይተው አይኖሩም ።

በተፈጥሮአቸው ፈጣሪያቸውን የማመስገን ክብሩንና ጌትነቱን የመናፈቅ ጠባይ አላቸው ። ምስጋናቸው ፣ ጣዕመ ዝማሬአቸውና ማኅሌታቸው ይጣፍጣል ፣ አጥንትን ያለመልማል ፣ መንፈስን ያድሳል ፣ ሕይወትን ይቀድሳል ። (ቅዳሴ ማርያም)

www.ethiopianorthodox.org

«---አንዱንም አንዱም በመቀባበል (በማስተዛዘል) ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምስጋናህ ምድርን ሁሉ ሞላ እያለ ይጮህ ነበር ፤ ከጩኸቱም ድምፅ የተነሣ የመድረኩ መሠረት ተናወጠ ፤ ቤቱ ንም ጢስ ሞላበት» (ኢሳ - ፮ ፤ ፫—፬) ።

ቅዱሳን መላእክት በሰማይና በምድር ፤ በፈጣሪና በፍጡራን መካ ከል ለተልእኮ ይመላለሳሉ ፤ሥነ ፍጥረትን በየወገኑ ይጠብቃሉ ። የሰዎ ችን ልመና ፤ ምኞትና ምስናና ወደ እግዚአብሔር ፤ የእግዚአብሔርን ቸርነትና በረከት ወደ ሰዎች ያደርሳሉ ። ለፍጥረት ሁሉ ደኅንነትና ሰላም ይጸልያሉ ፤ ፈጣሪያቸውን ይማልዳሉ ። በአማላጅነታቸው የሚ ያምኑ ተራዳኢነታቸውን የሚሹ ሁሉ በምድራዊ ሕይወት በሰላም እን ዲኖሩ ፤ በዓለመ ነፍስ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲወርሱ ለመርዳት ከእ ግዚአብሔር ዘንድ ሥልጣንና ባለሟልነት ተሰጥቶአቸዋል ። (ዘፍ - ፳፰ ፤ ፲፪ ፤ ዳን - ፲ ፤ ፲ - ፲፱ ፤ ዮሐ - ፩ ፤ ፶፪ ፤ ዮሐ ፤ ፲ ፤ ፬ ፤ ዕብ - ፩ ፤፲፬።)

## የስማቸው ትርጉም

መልአክ በነጠላ ፤ መላእክት በብዙ በዕብራይስጥም በግዕዝም ተላኪ ፤ መልእክተኛ አገልጋይ ማለት ነው ። የአምላክ (የፈጣሪ) መልእ ክተኛ ፤ እግዚአብሔር በረድኤት በሚገኝበት ሁሉ የሚገኝ ማለትን ያመ ለክታል ፤ እግዚአብሔር በረድኤት በሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ ቅዱሳን መላእክት ይገኛሉ ። መላእክት በሚኖሩበትም ቦታ እግዚአብሔር ይኖ ራል ። ይህም ሲባል እግዚአብሔር በቦታና በጊዜ የሚወሰን አለመሆ ሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል ። መንፈሳቸውን ንጹሕ ያደረጉና የእግዚ አብሔርን ቸርነት የሚሹ ሁሉ በመላእክት ይጠብቃሉ ። ክብር ሞገስ ፤ ሀብትና በረከት ያገኛሉ ። (መዝ ፺ ፤ ፲፩-፲፪ ፤ ሉቃ- ፩ ፤ ፺ ።

እያንዳንዱ ሰው በቀንና በሌሊት የሚጠብቀው (ጠባቂ) መልአክ አለው ሃይማኖቱ ጽኑ ምግባሩ መልካም የሆነውን ሰው ቀርቦ ይጠብ ቀዋል በችግሩ በጭንቁ ጊዜ ሁሉ ይረዳዋል ፤ ልመናውን ምስጋናውን ወደእግዚአብሔር ያደርስለታል ዕድሜውን ጤንነቱን ሀብቱን በረከቱን ይለምንለታል ሃይማኖቱን የሚክድ የሚጠራጠርምየሚያንጎራጉር ምግ ባረ ብልሹ ሰው የሆነ እንደሆነ ባይቀርቡትም ግዴታቸው ነውና ርቀው ይጠብቁታል ግን እንደበጐው ሰው አይረዱትም (ዳን ፩ ፲፫ ፲፯ ፤ ፲-፳፩ ፲፩ ፤ ፩ ፤ ፲፪ ፤ ፩ ማቴ ፲፰ ፲ ፤ ዕብ ፩ ፲፬)

የመላእክት ኅብረ መልክእ ይህ ነው ብሎ በተወሰነ ሥዕል መግ ለጽ እጅግ ያስቸግራል ። በተፈጥሮአቸው ረቂቃን ናቸውና ። ሆኖም



በሰው አቋም መልክና ቅርጽ እንደሚገለጹ ቅዱሳት መጻሕፍት ይገል ጻሉ ። ለምሕረትም ለመዓትም በሚገለጹበት ጊዜ በሰብአዊ መልክና አካል ይታያሉ ። በሰዎች ቋንቋም ይናገራሉ ። የራሳቸው ቋንቋ አላቸው ። በተልእኮአቸው ጊዜ ግን የሚናገሩት በተላኩ በት አካባቢ ሰው ቋንቋ ነው ። ዳን ፤ ፲ ፤ ፰ — ፳፩ ፤ ፩ ቆሮ ፤ ፲፫ ፤ ፩)

## ለቅዱሳን መላእክት የሚገባ የአክብሮት ስግደት

እግዚአብሔር በረድኤት በሚገኝበትና ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ፤ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ ቅዱሳን መላእክት በሚገለጹበት ፤ ድም ፃቸው በሚሰማበት ቦታ ሁሉ ለጌታ የባሕርይ የአምልኮ ፤ ለመላእክት የጸጋ የአክብሮት ስግደት ማቅረብ የተለመደ ነው ። ይህንንም (ዘኁ - ፳፪ ፤ ፴፩ ፤ ዘዐ ፤ ፳፫ ፤ ፳ ፤ ኢያ ፤ ፭ ፤ ፲፫ — ፲፭ መመልከት ይቻላል ።

ቅዱሳን መላእክት ኃያላን ግሩማን ስለሆኑ ሲገለጹ ግርማቸው ፤ ሲናገሩ ድምፃቸው ያስፈራል ,ያስደነግጣል ። የእግዚአብሔር ክብር ይገ ለጽባቸዋል ። ስለሆነም የጸጋ የአክብሮት ስግደት ይሰገድላቸዋል ። (ዳን ፲ ፤ ፱ ፤ የሐዋ-፲ ፤ ፬ ፤ ዳን - ፰ ፤ ፲፭-፲፯ ፤ ራእ - ፳፪ ፤ ፰ ። )

ስንኳን ለቅዱሳን መላእክት ከሰዎችም በሥራቸው መላእክትን ለመሰሉ ቅዱሳን የአክብሮት ስግደት ይሰጣል ፤ እግዚአብሔር የወደዳቸ ውንና ያከበራቸውን መውደድ ማክበር ይገባል ። (ዮሐ ፤ ፲፭ ፤ ፲፭ ።)

## ቅዱስ ገብርኤል

ጌታ መላእክትን ፈጥሮ በነገድ መቶ በከተማ ፲ አድርጎ በዓለማቸው እንዳዘጋቸው ተገልጧል ። ከመቶው ነገድ አንዱ ሳጥናኤልና ሠራዊቱ በትዕቢትና በክህደት ከክብራቸው ተዋርደው ፤ ከማኅበረ መላእክት ተለይተዋል ። ከግብራቸው አንጻር ዲያብሎስ ፤ ሰይጣን ፤ ጋኔን በመባል ስማቸው ተለውጦ ጨለማን ወርሰው እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል ። የሐ ሰት ፤ የትዕቢት ፤ የስስት የክህደትና የተንኮል ሥራ ሁሉ መሪዎች ስለ ሆኑ ሰውን ሲያሳስቱ በጨለማ መንገድ ሲመሩ ከእግዚአብሔር ሲያጣ ሉና ሲያካስሱ ይኖራሉ ። (ዮሐ ፤ ፰ ፤ ፵፬ ፤ ማቴ - ፲፫ ፤ ፳፰ ፤ ራእ -፲፪ ፤ ፱ ። ) ከማኅበረ መላእክት በተለየው መቶኛ ነገድ ቦታ የሰው ልጅ ገብ ቶበታል ።



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ ነቢያት ሄኖክ ስማቸውን በዝርዝር ገልጾ ከጻፋቸው ሊቃነ መላእክት አንዱ ቅዱስ ገብርኤል ነው ። (ሄኖ . ፫ ፣ ፲፩) «ገብርኤል» ማለት «የእግዚአብሔርን ልጅ የሚመስል ፣ ጌታና አገልጋይ» ማለት ነው ። ቅዱስ ገብርኤል ከበጐ ተልእኮው አንጻር ገጹ ብሩህ ደስ የሚል በፊቱ የደስታ ምልክት የሚታይበት በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ክብር ፣ መወደድና ባለሟል ነት የተሰጠው ፣ ባለምሥራች ፣ ሊያድነን ወደኛ የመጣ ፣ የጌታን ልደት ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የነገራት ፣ የዓለም መድኅን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዕለት በቤተልሔም ለነበሩ እረኞች ደስታንና የምሥራችን የገለጸ ሲሆን ፣ በርእየተ ገጹ (መልኩና አቋሙ) ከጥሩ ሐር የተሠራ (የበፍታ) ልብስ ለብሶ ፣የአፌዝ ወርቅ ዝናር በወገቡ ታጥቆ የሚታይ ፣ አካሉ እንደ ብርሌ የጠራ ፊቱ እንደመብረቅ የሚያበራ ዓይኖቹ እንደሚንበለበል ፋና ፣ ክንዶቹና እግሮቹ እንደጋለ ነሐስ የሚንቦገቦጉ ፣ የቃሉ ድምፅ እንደብዙ ሕዝብ ድምጽ የሚያስገመግም ፣ ቅርጹና ቁመናው የሰው ልጅ የሚመስል የምሕረት መልአክ ነው ። ከሕፃናት ጋር እንደ ሕፃናት ፣ ከንጹሐን ጋር ንጹሕ ሆኖ ሰዎችን ይጠብቃል ፣ ስለ ሰዎች ሰላምና ድኅነት ይጸልያል ፣ ይማልዳል ። (ዳን . ፲ ፣ ፭ - ፯ ፣ ሕዝ - ፱ ፣ ፪ ። ) ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል በጥንተ ፍጥረት መላእክት ፈጣሪያቸውን ተመራምረው እንዲያገኙ የተሰጠውን ፈተና በማለፍ «ፈጣሪያችንን እስከምናገኘው በየአለንበት ጸንተን እንቁም» በማለት ቅዱሳን መላእክትን ከጥርጥርና ከክህደት ፣ ከፍርሃትና ሽብር ያረጋጋ ፣ በእምነት እንዲጸኑ ያደረገ መልአክ ነው ። ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናዒና ኃያል ለምሕረትና ለይቅርታ ፈጣን ነው ። በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እየሰገደ ለሰው ልጆች ሁሉ ድኅነትን ፣ ይቅርታን ፣ ምሕረትንና በረከትን ያሰጣል ። ከፈጣሪ የሚገኘውን መልካም የምሥራች ሁሉ ወደ ሰው ልጆች ፈጥኖ ያደርሳል ። በችግር በጭንቅና የፈተና ጊዜ ሁሉ ደርሶ ይታደጋል ። (ዳን ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፣ ፱ ፣ ፳ ፣ ፲፱ ፣ ሉቃ - ፩ ፣ ፲፫ ፣ ፲፱ ና ፴)።

የቅዱሳን መላእክት አገልግሎትና ተልእኮ ፣ አማላጅነትና ተራዳኢነት በብሉያትና በሐዲሳት ፣ በሊቃውንት መጻሕፍትና በየድርሳናቱ በሰፊው ተገልጾአል ። ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል በቤተ ክርስቲያናችን በየወሩ ፲፱ኛ ቀን ይታሰባል ። በተለይ ታኅሣሥ ፲፱ ፣ ፳፪ና ሐምሌ ፲፱ ቀን ዓመታዊ በዓሉ በታላቅ መንፈሳዊ ድምቀት ይከበራል ። የመልአኩን አማላጅነት ፣ ተራዳኢነትና ታዳጊነት ያመኑ በስሙ የተማፀኑ ምእመናን በየቦታው በስሙ በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በብዛት እየተገኙ ፣ በዕልልታ በደስታና በመንፈሳዊ ተመስጦ ያከብሩታል

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን የሚከበርበት ምክንያት ሊቀ መላእክት ሆኖ ከእግዚአብሔር የተሾመበትን ዕለት ለማስታወስ ሲሆን በተጨማሪ ፣



፩ አናንያ ወይም ሲድራቅ
፪ አዛርያ ወይም ሚሳቅ
፫ ሚሳኤል ወይም አብደናጎ የተባሉ

ሦስት ወጣቶችን ከእሳት ያዳነበትን አስደናቂ ታሪክ በማሰብ ነው ።ሦስቱ ወጣቶች ፣ ወጣቱ ነቢይ ዳንኤልን ጨምሮ በናቡከደነጾር ከኢየሩሳሌም ተማርከው በጥንቱ ፋርስ ባቢሎን የተወሰዱ ናቸው ። ሦስቱ ወጣቶች ወደ እሳት ፣ ዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ የተጣሉት ንጉሡ ናቡከደነጾር በእብሪት (አምባገነንንነት) ላሠራው ጣኦት አንሰግድም ፣ ሕይወት የሌለው ሰው ሠራሽ አምላክ አናመልክም በማለታቸው ነው ። በከሳሾቻቸው የቀረበባቸውም ወንጀል ፣

- የንጉሡን ትዕዛዝ አይቀበሉም ፣ እንቢተኞች ናቸው ።
- ንጉሥ ያቆመውን አምላክ አናመልክም ብለዋል ።
- ለወርቁ ጣኦትና (ሰው ሠራሽ) ምስል አይሰግዱም የሚልነው

እሳቱ በመንግሥት ትእዛዝ በዐዋጅ ተሰብስቦ በተከመረ ዕንጨት የነደደና ወላፈኑ ሊያስቀርብ የማይችል እንደነበረ ተጽፎአል ። ነዲዱንም በበረታ ሁኔታ ማቀጣጠል የሚችሉ የሰምነት ጠባይ ያላቸው (እንደሞይደር) ወተት ያላቸውን ዕንጨቶች ተጨምረውበታል ። ልብሶቻቸውም በጥንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ማኅበረሰብ የአለባበስ ልምድ እሳት ከሩቁ የመሳብ ጠባይ ያላቸውና በሰውነት ላይ ተጣብቀው እንደ ሰም የሚቀልጡ ነበሩ ። ይህ ሁሉ ሆኖ በችግርና በመከራ ያልተለወጠው እምነታቸው የቃጠሎውን ኃይል የተከላከለው ስለሆነ ከእሳቱ የወጡት የጢስ ሽታ እንኳ ሳይሰማቸው ነው ። መልአከ እግዚአብሔር ቅ/ገብርኤል ከነሱ ጋር ነበረና ። እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ጠበቃቸው ፣ አዳናቸው ። የቃጠሎውን ትርኢት ለመመልከት በዙሪያው ተሰብስቦ ከነበረው ሕዝብ ብዙዎቹን የእሳቱ ወላፈን (የነበልባሉ) ኃይል እየጠለፈ ለብልቦዋቸዋል ።

# ቅዱስ ገብርኤል በቤተ መቅደስ

«እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ » (ሉቃ ፣፩፣ ፲፱ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእግዚአብሔር ወዳጆች እየተላከ ግዳጃቸውን ችግራቸውን የሚያቃልል ፈጣንና ረቂቅ ፣ ርኅሩኅና ተራዳኢ መልአክ መሆኑ በብዙ ቃላት ተገልጾአል ፣ በተጨማሪ ከዚህ ላይ ለመግለጽ የምንፈልገው ደግሞ ለዘካርያስና ኤልሳቤጥ ያደረገውን አገልግሎት ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ትባላለች ሁለቱም በሕገ እግዚአብሔር ተወስነው ትእዛዙን አክብረው ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ይኖሩ ነበር ሁለቱ በዕድሜ የገፉ ቢሆኑም ልጅ አልነበራቸውም ዘካርያስ እንደ ካህናት ሥርዓት በተራው ወደቤተ መቅደስ ገብቶ ሲያጥን ሕዝቡ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር ።

የጌታ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል በዕጣኑ መሠዊያ በስተቀኝ ቁሞ ታየው ዘካርያስም በተመለከተው ጊዜ በጣም ደነገጠ ፤ ፍርሃትም ያዘው ፤ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል ። ከእስራኤል ልጆች ብዙዎችን ወደጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል ፤ እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝቦች ለጌታ እንዲያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል ሲል ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ አበሠረው ።

ዘካርያስም መልአኩን እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ አለው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም መልሶ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ እንድነግርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ ይህ ነገር እስከሚፈጸም ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው ።

የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ቃል በማስተሐቀሩ (ባለመቀበሉ) ዮሐንስ ተፀንሶ እስከሚወለድ ድረስ ዲዳ ሆኖ ኑሮ በተወለደ ጊዜ አንደበቱ ረቶለት አፉ ተከፍቶለት ለመናገር ችሏል ፤ የእግዚአብሔር ባለሟሎች የሆኑትን የቅዱሳን መላእክትን ቃል የማይቀበል ሁሉ ፤ እንደዘካርያስ ያለ ቅጣት ይደርስበታል (ሉቃስ ፩ ፰-፳፫) ።

፪/ ታኅሣሥ ፳፪ ቀን የሚከበረው የተነገረው ትንቢት የተቈጠረው ሱባዔ ሲደርስ ዓለምን ለማዳን በዓለም የተገለጸው መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደሚወለድ ብሥራቱን የተናገረበት ታላቅ የምሥራች ቀን በመሆኑ ነው ። (ሉቃ፣ ፩ ፣ ፳፮) ይህ ዕለት በሞት ጥላ ውስጥ ለወደቀውና በጨለማ ለኖረው ሕዝብ የአዲስ ሕይወት መሠረት የተጣለበት ስለሆነ ለክርስቲያን ሁሉ የምሥራች ቀን ነው ። በዓሉ መከበር የነበረበት መጋቢት ፳፱ ቀን ሲሆን ታኅሣሥ ፳፪ ቀን እንዲከበር የተደረገው በአበው ውሳኔ ነው ።



፫/ ሐምሌ ፲፱ ቀን የ፫ ዓመቱ ፤ ሕፃን ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ሃይማኖታቸውን እንዲክዱ ፤ ለጣኦት እንዲሰግዱ የቀረበውን ጥያቄ ባለመቀበል በንፍር ውሃ እንዲቀቀሉ አላውያን ካስተላለፉባቸው ፍርድ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ያዳነበት ዕለት ነው ።

ሠለስቱ ደቂቅ (ሦስቱ ወጣቶች) እሳት ውስጥ በተጣሉበት ቀን በሰገነት ላይ ሆኖ ድርጊቱን ይመለከት የነበረው ንጉሥ እጅ እግራቸው ታስሮ እሳት ውስጥ ተጥለው የነበሩት ወጣቶች ሠንሰለታቸው ወልቆ በአቋሙ እነሱን የሚመስል ሌላ አራተኛ ወገን በመካከላቸው ሆኖ በሚንቦገቦገው እሳት ውስጥ ሲመላለሱ ተመልክቶ «እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ ። ምንም አልነካቸውም የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል» በማለት የተአምራቱን ሥራ መስክሯል ። በዚህም የወጣቶቹ ጽኑ እምነት ፤ የፈጣሪ ከሃሊነትና የመላእክት ተራዳኢነት ተመስክሮአል ፤ ተረጋግጦአል ። ይህን የመሰለውን ምስክርነትና የሙዳን ጸጋ ማግኘት የሚቻለው በሃይማኖት ጽናት ስለሆነ ሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ያለውን አመለካከት ሳያቃልልና ሳያወላውል ሲገኝ የጠየቀው ሁሉ የሚፈጸም ስለሆነ ሦስቱን ወጣቶች በሃይማኖት ይምሰላቸው በግብር ይከተላቸው ።

## ማስተዋል

በሦስቱ ወጣቶች ፤ በዳንኤል ፤ በቂርቆስና ቅድስት ኢየሉጣ ላይ የደረሰውን ፈተና ሁሉም አልፈው ያገኙት ክብር አብሮ ለሃይማኖታውያን ወጣቶች ሁሉ ትልቅ ትምህርትና ምሳሌ ነው ። ዓይነቱና መጠኑ ፤ ክብደቱና ሚዛኑ ይለያይ እንጂ ችግርና ፈተና ፤ እሳትና ጭንቅ በየጊዜው አለ ፤ ይኖራል ። የሃይማኖት ጽናት የሌላቸው ደካሞች ሊዘልቁት የማይሉት የመከራ አቀበትም ያጋጥማል። ሕሊና በጭንቀት ሲባዝን ፤ አእምሮ በሀዛብ ሲናጥ፤ ናላ በትካዜ ሲናወጥ የመንፈስ እንቅስቃሴ ሲብረከረክ ፤ ያሰቡት ቀርቶ ያላሰቡት ፤ የተመኙት ቀርቶ ያላለሙት አስከፊ ፈተና ሲደቀን የሚያረጋጋ ፤ የሚያጽናና የሚታደግና ወደ ሰላም ደሴት የሚያሸጋግር ወዳጅ አስቀድሞ ማበጀት ያስፈልጋል ። ሦስቱ ወጣቶች በምርኮኛነት በተወሰዱበት አገር ቤተ መንግሥት ለመኖር ደስ የሚያሰኝ ምቾት ፤ ለመብላት የሚያስጎመዥ ምግብ ቀርቦላቸው ነበር ። ምግቡን አልበሉትም ምቾቱንም አልሳሱለትም ። የጣኦት አምላኪዎች ማዕድ ብለው ተጠይፈው ትተው ጥራ ጥሬ ነበር የመረጡት ። ጮማ በሸምብራ ጠጅ በውኃ ሲለወጥ ምን ጊዜም ብዙ ተመሳሳይ (ተወዳዳሪ) የማይገኝለት የቆራጥነት ታሪክ ነው ። እነ አናንያ ጥሬ በልተው ውኃ ጠጥተው በ

www.ethiopianorthodox.org

ውበታቸው በቤተ መንግሥቱ ከነበሩት ቅምጥሎች ያላነሰ እንዲያውም የበለጠ ሞገስና ጸጋ የሚታይበት ፣ ያለፉበት ጠባብ የሃይማኖት መንገድም በእሳት ተፈትኖ እንደሚጠራ ወርቅ ከፈተና እሳት እንደሚያድን ያስተምራል ። ከየት እንደመጡ ለምን እንደመጡ ፣ ምን ተልእኮ እንዳላቸው የምናውቃቸው የቀበሮ ባሕታውያን በመካከላችሁ እንስገድ የሕወትን መንገድ እንምራችሁ ይሉናል ፤ ያባብሉናል ፣ ይደልሉናል ፣ ጆሮ ያለው ይስማ ፣ አእምሮ ያለው ያስተውል ። መምህራን ነን የሚሉ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ተሸክመው የክርስትናን ስም አንግበው በየመንደሩ የሚዞሩ ፣ ሃይማኖት አመጣንላችሁ የሚሉ ሁሉ መምህራን አይደሉም ፣ መምህሮቻችንን መለየት ማወቅና መከተል ያስፈልጋል ።

የእኛ የምንለው የእኛነታችን መታወቂያ የሆነ ሐዋርያዊ ፣ ኦርቶዶክሳዊ እምነት ፣ ትውፊት ፣ ታሪክ ፣ ባህልና ሥርዓት አለን ። ሃይማኖት በችግር ወይም በምቾት ፣ በመከራ ወይም በደስታ አይለወጥም ። የሦስቱ ወጣቶች ታሪክ ብዙ ያስተምራል ። የኖሩት በስደት አገር በአምልኮ ጣኦት በረከሰ ሕዝብ መካከል ነው ። ምርኮኞች ነበሩ ። የወጣትነት ዕድሜ መከራን ታግሦ የሚያሳልፉበት ፣ ክፉንና በጎን አመዛዝኖ በፈተና ውስጥ በማለፍ ከመከራው የሚገኝ ጸጋንና ክብርን ለመጐናጸፍ ጠባቡን መንገድ የሚመርጥበት ወቅት አይደለም ። ችግሩ ይከብዳል ፈተናው ያስጨንቃል ፣ ደስታው ይስባል ፣ ያጓጓል ፣ ይማርካል ። ሠለስቱ ደቂቅ ግን ለመከራው አልተበገሩም ፣ ደስታውም አላሳሳታቸውም።በሃይማኖት ሁሉንም አሸንፈውታል ። እናቶቻቸው ያወጡላቸው ስም ተለውጧል ፣ ሃይማኖታቸው ግን በደስታውም በመከራውም አልተለወጠም ። ዳንኤል በጣዖት አምላኪዎች ቤተ መንግሥት ጊዜያዊ የምቾት ኑሮ ከመኖር ይልቅ የመረጠው በአንበሶች ጉድጓድ ተጥሎ ለሃይማኖት መሠዋትን ነበር ። በአንበሶች አልተበላም ጽኑዕ ሃይማኖቱ አድኖታል ። በሌላውም ፈተናው ሁሉ የእግዚአብሔር መልአክ አልተለየውም ። ቅዱስ ገብርኤል ከእሱ ጋር ነበር ። ጥበብና ማስተዋልንም አስተምሮታል ። የእምነቱ ጽናት መከራውን ሁሉ አሳልፎለታል ። ሌላው ምርኮኛ ጠላት በየምክንያቱ እየገደለ የሚጥላቸውን የወገኖቹን አስከሬን በድብቅ እየሰበሰበ በመቅበር ከአሞራና ከአራዊት አፍ ያድን የነበረው ጦቢት በቅን አገልግሎቱ ጊዜ በደረሰበት የዓይን መታወክ ለጊዜው ቢፈተንም በእምነቱ ጽናት ነፃነቱንና የዓይኑን ብርሃን አግኝቷል ። ሕፃኑ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስም እናቱን ጭምር እያበረታታ በሃይማኖት የመጣበትን ችግርና ፈተና ተቋቁሞ በማለፉ ለክርስቲያኖች ሁሉ መልካም ምሳሌ ሆኖ ሲታሰብበት ይኖራል ። (የሐ ፣ ሥ ፣ ፩ ፣ ፳፱ ።)

ሁሉም ወጣቶች «ከሰው ይልቅ ለእግሊአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» በሚለው መርህ በመጽናት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጠው በተጋድሏቸው መንግሥታትን ድል ነሡ ፣ ጽድቅን አደረጉ ፣ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ ፣ የአንበሶችን አፍ ዘጉ ፣ የእሳትን ኃይል አጠፉ ፣ ከሰይፍ ስለት አመለጡ ፣ ከድካማቸው በረቱ ፣ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ ፣ የባሮች ጭፍሮችን በተኑ ። (ዕብ ፣ ፲፩ ፣ ፴፫-፴፭) ። በዚህም ምክንያት በዚህ ዓለም ዝክረ ስማቸው በመልካም ሲወሳ ታሪካቸው ሲነበብ መታሰቢያው ሲከበር ይኖራል ። በወዲያኛውም ዓለም ለአሸናፊዎች ሁሉ የተዘጋጀው ዋጋና ክብር ይጠብቃቸዋል ። ሕይወታቸው በሁለት ዓለማት የከበረች ናት ።

እኛም በዚሁ የጽድቅና የሕይወት መንደድ ለመጓዝ «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ? መከራ ወይስ ጭንቀት ? ስደት?ረሀብ ? ራቁትነት ? ፍርሃት ? ወይስ ሰይፍ ነውን ? » እያልን ከዓለም ወገን የሚመጣውን ችግርና ፈተና በእምነት በመቋቋም የክብር ባለቤቶች እንድንሆን ያስፈልጋል ። ሮሜ ፣ ፰ ፣ ፴፩—፴፱ ። )

## ስእለት (ብፅዓት)

ስእለት (ብፅዓት) ለቤተ እግዚአብሔር በበጎ ፈቃድ የሚቀርብ ስጦታ ነው ። ሰዎች ስእለት የሚሳሉት በሕመም ፣ በአደጋ በችግርና በጭንቅ ጊዜ ከገጠማቸው ችግር ለመዳን ነው ። ከእግዚአብሔር ለሚያገኙት የበረከት ስጦታ ወይም እግዚአብሔር ያስቡትንና የተመኙትን እንዲሰጣቸው በማመን ይህን ባገኝ ይህን አደርጋለሁ ! እሰጣለሁ ! » ብለው ቃል ይገባሉ ። የልጅ ጸጋ ፣ የሕሊና ሰላም በማጣት ፤ በስደትና በምርኮ በመንከራተት በሀብትና በጤንነት ፣ በዕውቀትና የቤተሰብ ሕይወት በመሳሰለውም ሁሉ ከሚገጥም ችግር ለመውጣት ሰዎች የዕድሜ ልክ አገልግሎት ለማቅረብ ፣ ልጆቻቸውንና ሕይወታቸውን እንኳ ሳይቀር ለእግዚአብሔር ለመስጠት ቃል ይገባሉ ። ስእለት በግልጽም በምሥጢርም ይፈጸማል ።

## የሚገባ ስእለት

«በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቴን ለእግዚአብሔር እሰጣለሁ» (መዝ ፣ ፻፲፭ ፣ ፲፬) በምንሳልበት ጊዜ ልንሳለው የሚገባውንና የማይገባውን ሳንመረምር ከጭንቀታችን (ከደስታችን) የተነሣ በችኮላ መሳል የለብንም ። ከማንወጣው ሌላችግር(ዕዳ)ውስጥ እንዳንገባ በብርቱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። እግዚአብሔርንም መፈታተን ፣ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ስእለታችን በእህል ፡ በገንዘብ ፡ በእንስሳት ፡ በወርቅ በማዕድር ፡ በልብስ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ዕቃዎች በሙብልና መጠጥ በምጽዋት - - - ሊሆን ይችላል ።

ሁሉም ለገባንበት ቃል የተቀደሰ ስጦታ ነው ። የሚያገለግለውም ለቤተ እግዚአብሔርና በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ እንዲያገለግሉ ለተ ፈቀደላቸው ወገኖች ነው ። ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳን ቃል ከተገባው የስእለት ገንዘብ (ሀብት) ዓይነቱ መጠኑ አይሻሻልም ፡ መልካሙ በመ ጥፎ መጥፎ በመልካም አይለወጥም ። ስእለትና ብጽዓት ሁሉ በፈቃድ የሚደረግ ነው ። ማንም ሰው እንዲሳል (ብፅዓት) እንዲያደርግ አይገደ ድም ። ይህም በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ክፍሎች ተገልጾአል ።

አንድ ሰው ከተሳለና ብፅዓት ካደረገ በኋላ ቃሉን ጠብቆ ግዴታውን መፈጸም አለበት ። «ሰው ለእግዚአብሔር ስእለት ቢሳል ወይም ራሱን በመሐላ ቢያስር ቃሉን አይስበር ካፉ እንደወጣው ሁሉ ያድርግ ።» (ዘኍ ፡ ፴ ፡ ፪ ።)

ነቢዩ ሙሴ ይህንኑ ቃል በማጽናት በዳግም ሕግ «ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር ካንተ ፈጽሞ ይሻዋልና ኃጢአትም ይሆንብሃልና መክፈሉን አታዘግይ ፡ ሳት ሳል ግን ኃጢአት የለብህም በአፍህ የተናገርከውን ለአምላክህ ለእግዚ አብሔር በፈቃድህ ተስለሃልና ከከንፈርህ የወጣውን ታደርግ ዘንድ ጠብቅ» ብሏል ። (ዘዳ ፡ ፳፫ ፡ ፳፩ ።)

ሰሎሞንም «ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ ፡ የተሳልሽውን ፈጽመው ፡ ተስለህ የማትፈጽመው ብት ሆን ግን ባትሳል ይሻልሃል ፡ ሥጋህን በኃጢአት እንዳያስተው ለአፍህ አርነት ስትሰጥ በመልአክም ፊት ስሕተት ነበር አትበል ። እግዚአብሔር ይቆጣ ዘንድ የእጅህንም ሥራ ያጠፋ ዘንድ ስለምን ትሽለህ ? » በማለት ጽፎአል ። (መክ ፡ ፭ ፡ ፬—፮ ።)

ቅዱስ ዳዊት የአንድ እውነተኛ ሰው መለያ ከሆኑ ጠባዮች አንዱ የተናገሩትን ቃል መጠበቅና መፈጸም ነው ። ባህላዊው አገላለጣችንም «የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ» የሚል ነው ። ይህም ቁም ነገርን (ቃልን) መጠበቅ ታላቅ ነገር መሆኑን ያመለክታል ። (መዝ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭፡፬።

## የተለመዱ ዓይነት ስእለቶች

ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ሸሽቶ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን በተሰደደ ጊዜ ድንጋይ ተንተርሶ በብቸኝነት ፡ በጭንቅና በፍርሃት ባደረበት በታ

«እግዚአብሔር ከኔ ጋር ቢሆን ፡ በምሄድባትም በዚች መንገድ ቢጠብ ቀኝ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ እግዚአብሔር አምላኪየ ይሆንልኛል ፡ ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል ፡ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከዐሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ» ብሎ ተሳለ (ዘፍ ፡ ፳፰፡ ፳—፳፪) ።

ሐና ልጅ ሳትወልድ በመካንነት ብዙ በመቆየቷ ታዝን በልቧም ትመረር ነበር ። ጽኑ ልቅሶም አልቅሳለች ። አንደበቷ ሳይናገር የኀዘን ዕን ባዋን ከስሜቷ ምንጭ እየቀዳች በጉንጮቿ ላይ ስታፈስ ኖራለች ።» የወ ይን ጠጅ ጠጥታለች» የተባለችበትና እንደስካር የተቆጠረችበትም ጊዜ ነበር ። በሁሉም ባልወለዱ መካን ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማናቸውንም ሐሜትና ዘለፋ ተቋቁማ በሃይማኖት ጸሎት ፈጣሪዋን ደጅ በመጥናቷ የተመኘችውን አግኝታለች ። በጸሎቷ «አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ ! የባ ሪያህን መዋረድ ተመልክተህ ብታስበኝ እኔንም ባትረሳ ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ» ብላ ልጅዋን ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት በመስጠት ተሳለች ። እግዚአብ ሔርም ልመናዋን ሰማ ፡ ስእለቷን ተቀብሎ የተመኘችውን እንድታገኝ አደረገ ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የታወቀ ነቢይ ሳሙኤልን ያህል ታላቅ ሰው ወለደች ። (፩ ፡ ሳሙ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯-፳፰ ።)

ሕልቃና ሚስቱ ሐና የመውለጃዋ ዘመን ካለፈ በኋላ በእርጅና ጊዜዋ ወንድ ልጅ በመውለዷ መሥዋዕቱንና ስእለቱን ለእግዚአብሔር እንዳቀረበ ተጽፎአል ። (፩ ፡ ሳሙ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ።)

ቅዱስ ዳዊት በትንቢት የተገለጸለትን የሥጋዌ ምሥጢር ፍጻሜ በመሻት በተሳለው ስእለትና በማለው መሐላ «እውነት ወደቤቴ ድን ኳን አልገባም ፡ ወደ አልጋዬ ምንጣፍም አልወጣም ፡ ለዓይኖቼ ዕንቅ ፍን ለሽፋሽፍቶቼም ሽልብታን ለጉንጮቼ ዕረፍትን አልሰጥም ፡ ለያዕ ቆብ አምላክ ማደሪያ (የተወለደበትን ቦታ) እስካገኝ ድረስ» ብሏል ። (መዝ ፡ ፻፴፩/፻፴፪/፫—፭ ።)

ነቢዩ ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት ኮብልሎ ለማምለጥ ባደረገው ሙከራ ወደ ባሕር ተጥሎ በዓሣ አንበሪ በተዋጠ ጊዜ በሞትና በሕይወት መካከል በነበረች ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ በገባው ቃል «ነፍሴ በዛለችብኝ ጊዜ እግዚአብሔርን አሰብሁት ጸሎቴ ወደ አንተ ወደ ቅዱስ መቅደስ ገባች ከንቱነትንና ሐሰትን የሚጠብቁ ምሕረታቸውን ትተዋል፣ እኔ ግን በምስጋና ቃል እሠዋልሃለሁ ፡ የተሳልሁትንም እከፍላለሁ» በማ ለት በጭንቁ ጊዜ ስእለት መሳሉን ፡ የምሕረት አምላክ እግዚአብሔርም ጸሎቱንና ስእለቱን ተቀብሎ ዓሣውን እንዳዘዘው እሱም ዮናስን በየብስ

www.ethiopianorthodox.org

(ደረቅ ምድር) ላይ አውጥቶ እንደተፋው ተጽፎአል ። (ዮና ፡ ፪ ፡ ፱—፲፩።)
ቅዱስ ጳውሎስ ባደረገው ብፅዓት በባሕር በመርከብ ተጭኖ ወደ
ሶርያ በሄደ ጊዜ በክንክራኦስ ራሱን እንደተላጨ የሐዋርያት ሥራ ይና
ገራል ። (የሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰ ።)

# ተገቢ ያልሆነ ስእለት (ብፅዓት)

ሰዎች የሚሳሉት በአመዛኙ በችግር ጊዜ ነው ። ችግር ያስጨን
ቃል ። ጭንቀትም ያስቸኩላል ፡ በችኮላ የሚነገር ቃል ደግሞ ስሕተት
ላይ ይጥላል ። ስእለታችንና ብፅዓታችን በችኮላ የምንናገረው እንዳይሆ
ንና ጸጸት ላይ እንዳንወድቅ በብርቱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

አንድ ሰው ለጸሎቱ ምላሽ ወይም የተመኘውን ለማግኘት አስፈ
ላጊ ያልሆነ ስእለት መሳል ወይም ሊፈጽሙት የሚከብድ ብፅአት ማድ
ፈግ የለበትም ። የችግሩን ክብደትና መጠን አይቶ ተመኝቶ ከሚያገኘው
ነገር የማይቀራረብ የቃል ዐሥራት ውስጥ መግባት አደገኛ ነው ። የሚ
ያስቸኩል ፡ የሚያቅበጠብጥና በቃል የተነሣ በጥፋት ወጥመድ ውስጥ
እንዲገቡ የሚያስገድድ ኃይል አይኖርም ።

በዚህ መልኩ ከተፈጸሙ የስሕተት ሥራዎች የዮፍታሄን ታሪክ በም
ሳሌነት ማቅረብ ይቻላል ።

«ዮፍታሔ በውነት የአሞንን ልጆች በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠኝ
በደህና ብመለስ ሊገናኘን ከቤቴ ደጅ የሚመጣው ማንኛውም ለእግዚአ
ብሔር ይሆናል ። ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቀርበዋለሁ» ብሎ ለእግ
ዚአብሔር ስእለት ተሳለ ፡ ሊዋጋም ወደ አሞን ልጆች አለፈ ። እግዚአ
ብሔርም በእጁ አሳልፎ ሰጠው - - - ሃያ ከተሞችን በታላቅ አገዳደል መታ
ቸው ። የአሞንም ልጆች በእሥራኤል ፊት ተዋረዱ ። ዮፍታሄም ወደ
ቤቱ ተመለሰ ፡ እነሆም ልጁ አታሞ ይዛ እየዘፈነች ልትቀበለው ወጣች፤
ለርሱም አንዲት ብቻ ነበረች ፡ ከርሷም በቀር ወንድ ወይም ሴት ሌላ
ልጅ አልነበረውም እሷንም ባየ ጊዜ ልብሱን ቀደደ ፡ አወይ ልጄ ሆይ
ወደ እግዚአብሔር አፌን ከፍቻለሁና ፡ ከዚያውም እመለስ ዘንድ አል
ችልምና በጣም አዋረድሽኝ ፡ አስጨነቅሽኝም አላት ፡ እርሷም አባቴ ሆይ
አፍህን ለእግዚአብሔር ከከፈትህ እግዚአብሔር ተበቅሎልሃልና እንደ
ተናገርህ አድርግብኝ ፡ ግን ወደ ተራራ ወጥቼ ከባልንጀሮቼ ጋር ለድን
ግልናዬ እንዳለቅስ ሁለት ወር አሰናብተኝ አለችው ። አሰናበታት ከባል
ልንጀሮቿም ሄዳች በተራሮችም ላይ ለቁንጅናዋ (ድንግልናዋ) አለቀሰች፤
ሁለትም ወር ከተፈጸመ በኋላ ወደ አባትዋ ተመለሰች እንደተሳለውም

ስእለት አደረገባት ፡ እርስዋም ወንድ አላወቀችም ነበር ። የእሥራኤልም
ሴቶች ልጆች በዓመት በዓመቱ እየሄዱ የገለዓዳዊውን የዮፍታሄን ልጅ
የአራት ቀን ሙሾ እንዲያወጡ ልማድ ሆነ ።

ዮፍታሄ በጠላቶቹ ላይ ድልን ለማግኘት እግዚአብሔርን በእምነት
ብቻ መማጠን አልያም ለምኞቱ ተመጣጣኝ የሆነ ስእለት መሳል (ብፅ
አት ማድረግ) ይችል ነበር ። እግዚአብሔርም የለመኑትን የማይነሳ የነ
ገሩትን የማይረሳ ከሐሴ ኰሉ (አልሻዳይ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው) አም
ላክ ስለሆነ የተመኘውን ያደርግለት ነበር ። አሰቃቂ ታሪኩ ለሁላችን
ትምህርት ይሆን ዘንድ ተጽፎአል ። (መገ ፡ ፲፩ ፡ ፳፱-፵ ።)

ለእግዚአብሔርም ሆነ እሱን በማገልገል ለከበሩ ቅዱሳን የምንሳ
ለው ስእለትና የምናደርገው ብፅዓት በገንዘብና በቁሳቁስ ብቻ እንዲሆን
የሚያስገድድ ነገር አይኖርም ። ከማይቋረጠው የዘወትር ምስጋና ልየት
ባለ አዲስ ምስጋና ልናቀርብ እንችላለን ። በሕይወታችን ለሚደረገልን
በጎ ስጦታ ሁሉ የምስጋና መሥዋዕት ማቅረብ አለብን ። እግዚአብሔር
ከኛ የሚፈልገው ንጹሕ ሕሊና ቀና መንፈስ ፡ የማያወላውል እምነትና
በፍቅር የታነጸ ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው ። (መዝ ፡ ፶፬ ፡ ፩ ።)

ብዙ ሰዎች ለቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ይሳላሉ ፡ የስእለታቸውም ዓይ
ነት ልዩ ልዩ ነው ። ወርቁ ፡ ብሩ ፡ ጧፉ ፡ ዕጣኑ፡ የአበባ ምንጣፉ ፡ ሠን
ጋው ሙክቱ ፡ ዶሮው ፡ ፍየሉ ፡ ጃንጥላው ፡ አልባሳቱ ስንቱ ስንቱ ብዙ
ነው ። ሁሉም መልካም ነው ፡ ለቤተ ክርስቲያን ያገለግላል ። በጣም የሚ
ገርመው ግን ለጥፋት ካልሆነ በቀር ለምንም ዓይነት አገልግሎት የማይ
ውሉ የስጦታ አይነቶችንም የሚያቀርቡ ሰዎች መኖራቸው ነው ። አን
ዳንዶችንም በስማቸው ለመጥራትም እንኳ ይከብዳል ፡ ያስጸይፉል ፡
ለቤተ እግዚአብሔር በስእለት ሊቀርቡ ይቅርና ከመኖሪያ አካባቢም
እንዲጠፉ ሌላ ስእለት የሚደረግባቸው የቤት ውስጥ ጠላቶች ናቸው ።
የማያስፈልግ ፡ ጨርሶም የማይገባ መሆኑን ለመግለጽና ለማስተማር ስለ
ሆነ ብቻ ጥቂቶችን መጥቀስ ግድ ይሆናል ።

ለምሳሌ ፡ አይጥ ፡ እባብ ፡ እንቁራሪት ፡ - - የመሳሰሉትም ሌሎች
ሁሉ ሊነገሩ ሊታዩ ቀርቶ ሊታሰቡና ጆሮ ሊሰማቸው የማይገባ ብዙ አስ
ቀያሚ ነገሮች ። ከዚህም ሁሉ ጋር ብዙ ሰዎች ወደቁልቢ በአየርና በየ
ብስ የሚጓዙት ለንግድ ፡ ለመዝናናትና ከመንፈስሳዊ ዓላማ ውጭ ለሆነ
የማይገባ ሥራ መሆኑ በድርጊት ይታያል ። ወቅቱ የጾም ጊዜ ይሁን አይ
ሁን ሳይታሰብ ይታረዳል ። ይጠበሳል ፡ ይቀቀላል ይበላል ። የአልኮል
መጠጦች በየድንኳኑ ፡ በየጎጆውና በየዳሱ ያለ ልክና መጠን ይጠጣሉ ፡
«በልጅ አመካኝቶ - - - » እንዲሉ በብርድና በቅዝቃዜ እየተመካኘ አረቄ
ይጠጣል ። ሙዚቃው ያስተጋባል ፡ ዘፈኑ ጭፈራውና ዳንኪራው ዙሪ



www.ethiopianorthodox.org

ያውን ይቀልጣል ። ሌላም ሌላም ፤ በቤተ እግዚአብሔር አካባቢ ሊፈ
ጸም የማይገባው አስነዋሪ ሥራ ሁሉ እንዳለ ይታወቃል ። ይህም ፤ የሃ
ይማኖትን ድንጋጌ ፤ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና ቀኖና መጣስ ፤ ማበላ
ሸት እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል ። አንዳንድ ሰዎች «ይህን አድርጉ»
ተብለው የሚገደዱ ይመስል «ይህን ያህል ኪሎ ሜትር በእግሬ እንዛ
ለሁ» «ራቁቴን በጉልበቴ ተንንብሼ በቤተ መቅደስህ ዙሪያ እዞራለሁ»
«- - - ወዘተ እያሉ በመሳል በመንገድ ላይ ለሚደርሱ አደጋዎች ራሳቸ
ውን የሚያጋልጡ ፤ ሌላ ጊዜ ፩ ኪሎ ሜትር በእግራቸው ተጉዘው የማ
ያውቁ ልምምድ በሌለው ረጅም ጉዞ እግራቸው እስኪላላጥ የሚሰቃዩ ፤
በመንገድ ላይ በውኀ ጥም በራስ ምታት በድካምና በዝለት በየዛፉ ሥር
የሚወድቁ ብዙ ናቸው ። ከሁሉም ይልቅ እርቃናቸውን በቤተ ክርስ
ቲያን ዙሪያ በሕዝብ መካከል የሚዞሩ ሰዎች ሁኔታ በብዙ መልኩ ደስ
የሚል አይደለም ። ነገሩ የሰውነት ግብር ለማቅረብና ለስእለቱ ክብደት
ሰጥቶ የሚሹትን ለማግኘት መሆኑ ግልጽ ነው ። ሆኖም የአካልና የአእ
ምሮ ጭንቀት የሚፈጥር ስእለት እየተሳሉ ከሚደርሰው ችግር የተነሣ
ሌላ ፈተና መፍጠር ጉዳትን መሻት ነው ። እግዚአብሔርንም መፈታ
ተን ነው ። ጸሎታችን ፤ ስእለታችንና ብጽዓታችን ሁሉ ከንቱ እንዳይሆን
ከእምነቱ ፤ ከሥርዓቱና ትውፊቱ አኳያ ልናመዛዝነው ይገባል ። ለእኛ
ሊጠቅሙንና ሊያገለግሉን የማይችሉ ፤ ለቤተ እግዚአብሔር የማያገ
ለግሉ አራዊት ተባዮች አስቀያሚ ነገሮችን ማቅረብ ምን ይጠቅማል?
እግዚአብሔር ቅዱስ ነው የሚያስደስተው የተቀደሰ ነገር ነው ። ንጹሕ
ባሕርይ ነው የሚወደው ንጹሕ ነገርን እንደሆነ ማስተዋል ክርስቲያ
ናዊ ግዴታ ነው ። ስእለታችንና ብፅዓታችንን ሁሉ ከቃየልና ከአቤል
መሥዋዕት አኳያ በማመዛዘን ንጹሕ ነገርን ያቀረበውን አቤልን በመሥ
ዋዕቱ በንጹሕ አሳቡ ልንመስለው ይገባል ። (ዘፍ - ፬) ለጽድቅ ለምስ
ጋና ፤ ለቅድስና ተብሎ የሩቅና የቅርብ ጉዞ በሚደረግባቸው አብያተ ክር
ስቲያናት ዙሪያ የመብልና የመጠጥ ፤ የንግድና የመዝናናት ተግባር መፈ
ጸም «መክፈልት ሲሹ መቅሠፍት» መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል ።

«የምትረግጣት ምድር የተቀደሰች ናትና ጫማህን አውልቅ»ተብሎ
ቅድስናዋ የተጠበቀላትን ቤተ ክርስቲያን መዳፈር የሚያስከትለውን
ቁጣና መቅሰፍት በብርቱ ማሰብ ያስፈልጋል ።

ወደ ቁልቢም ሆነ ወደ ሌሎቹ ሥፍራዎች ለቅዱስ ገብርኤል የተ
ሳልነውን ስእለት ይዘን ስንሄድ በንጽሕና በቅድስና ተጠብቀን ያሰብነ
ውን ፤ የተመኘነውንና የጠየቅነውን በረከት ለመቀበል ብቁዎች ሆነን
መገኘት ይኖርብናል ። በተለይ በብካትና በስፋት በቁልቢ ቅዱስ ገብር
ኤል ገዳም በየዓመቱ የሚታየውን የመንፈሳዊ ዓላማ ተቃራኒ የሆነ ሥጋዊ
አስተሳሰብና በመብል መጠጥ ብዛት የሚታየውን ድርጊት ቤተ ክርስ
ቲያን አጥብቃ ትቃወማለች ፤ አይበላ አይጠጣ ማለት አይደለም ፤ ዓይ
ነቱ ፤ መጠኑና ከመብልና መጠጡ ጋር የሚታየው ዓለማዊ ሥራ ሁሉ
ሕግና ሥርዓትን ፤ ጊዜንና ቦታን መለየት ይኖርበታል ።

በመሠረቱ ለቤተ እግዚአብሔር ተገቢ ያልሆነና ጠቀሜታ የሌ
ለው ስእለት ማቅረብ ከምን የተገኘ ነው? ንጹሕ እምነትን ከልማድ ፤
ከአምልኮ ባዕድና ከአጉል አስተሳሰብ ለይቶ መከተል ያስፈልጋል ።
«ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ፤ ጽድቅ ከዓመፅ
ጋር ምን ተካፋይነት አለው ? ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?
ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማ
ያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔርን ታቦት ከጣዖት ጋር ምን
ያገናኘዋል? (፩ ቆሮ - ፮ ፤ ፲፬—፲፮ ። )

## የቅዱስ ገብርኤል ተአምር በዐፈርና በዛፍ ፍሬ ሳይቀር

በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የሚቆመው የእግዚአብሔር ባለሟል
ቅዱስ ገብርኤል አንድ ነው በስሙ የታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ስሙ
በሚጠራባቸው ሥፍራዎች የሚፈጸመው ገቢረ ተአምራት ግን ብዙ
ነው ።

ካህኑ በሰሞን ተራው ጸሎተ ዕጣኑን በሚያሳርግበት ጊዜ በዕጣኑ
መሠዊያ በስተቀኝ ቆሞ «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሀልና አትፍራ»
ብሎ የምሥራች ቃልን የነገረው የተነገረውን ቃል ፤ ምሥራች ተቀባዩ
ሰው ከግል ሁኔታው አኳያ በማገናዘብ እንደማይፈጸም በተከራከረ ጊዜ
«እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ ይህን የምሥራች
እንድነግርህ ተልኬአለሁ እነሆም በጊዜው ጊዜ የሚፈጸመውን ቃሌን
ስላላመንህ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም
አትችልም» በማለት የዘካርያስ አንደበት ተይዞ እንዲቆይ ያደረገው የመ
ላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ተአምራት ማድረግ ፤ የደስታን ዜና ማብ
ሠር ፤ የተቸገሩትን መርዳት የታመሙትን መፈወስ ከእግዚአብሔር የተ
ሰጠው ሥልጣኑ ስለሆነ ተአምራት የሚያሳይባቸው ቦታዎች ብዙ ናቸው

በሰሜን ሸዋ መንዝ ቀያ ጌራ የሚገኘው የሰዳዳ ቅዱስ ገብርኤል
አስደናቂ ተአምራት እያደረገነው መካኖች ተስለው በዓመቱ ልጅ አዝ
ለው ይሄዳሉ ። በሰይጣን ቁራኛ በአጋንንት አሽክላ የተተበተቡ ፤ በር
ኩሳን መናፍስት የሚንገላቱ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ፭ እና ፮ ኪሎ
ሜትር ርቀት ላይ ሲደርሱ ይጮሃሉ ። አንዳንዶቹ ከየቦታው በገመድና
በሰንሰለት ታስረው ሄደው እቦታው ሲደርሱ በሽታው ለቆአቸው በተ


www.ethiopianorthodox.org

ስተካከለ አእምሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ጤና ሆነው ይመለሳሉ። ሌሎች ለማኅሌትና ለቅዳሴ ደወል ሲደወል ይንሣባቸዋል በመስቀል ሲዳሰሱ ይድናሉ በግቢው የነበረውን ያኮሽም ዛፍ ፍሬ እየበሉ ይፈወሳሉ አሁን ፍሬው ብቻ ሳይሆን ቅጠሉም የግንዱ ቅርፊትም በእምነት እየተወሰደ ዛፉ ተበልቶ እስኪያልቅ ሕዝብ እየተሻማው ነው ዐፈሩን እየዘገኑ ሰውነታቸውን በማሸት የሚድኑም ጥቂቶች አይደሉም ። ከመሀል ሜዳ በግምት ወደ ምዕራብ ፳ ኪሎ ሜትር ላይ ይገኛል ። ሠላሳው ኪሎ ሜትር መኪና ይገባል እስከቦታውም ድረስ አልፎ አልፎ መኪኖች ይመላለሳሉ ዝርዝር ዜናውን በሚቀጥለው ጊዜ በሰፊው እናቀርባለን ።

## የጀር ቅ|ገብርኤል ታሪክና አስደናቂ ተአምር

ሥፍራ ቍጥር የሌላቸው ሕሙማን ከደዌያቸው የተፈወሱበትና የብዙዎች ዕውራን ዐይን የበራበት የጀር ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በብቸና አውራጃ ጥንታዊትና ባለታሪክ በሆነችው በደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም አጠገብ ነው ። ይህ ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን የሚገኝበት ቦታ ተራራማ በመሆኑ ከቦታው ላይ ሁነን ስንመለከት የጎጃምን ክልል በሙሉ የወሎን የጐንደርን የሸዋን የወለጋን ክልል በከፊል የሚያሳይ ማዕከለ ምድር የሆነ ቦታ ነው የዚህን ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በጽሑፍ ለመግለጽ በሚአዳግት እጹብ ድንቅ በሆነ ደን የተሸፈነና የተዋበ በመሆኑ በአካባቢው ያለው ውበትና ግርማ ምንጊዜም ከሕሊና የሚጠፋ አይደለም ።

የጀር ቅ/ ገብርኤል አዲሱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሁን በሚሠራበት ቦታ በዐፄ ገላውዴዮስ ዘመነ መንግሥት አካባቢ የቅዱስ ገብርኤል ታቦት ተተክሎበት ታላቅ ገዳም ሁኖ ቆይቷል በዚያ ጥንታዊ ዘመን በተራራማው ሥፍራ ላይ የጀር ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የተተከለበት ምክንያት በቅድስት እመቤታችን ድንግል ማርያም ስዕለ አድኅኖ ግራና ቀኝ የቅ/ሚካኤልና የቅ/ገብርኤል ሥዕሎች እንደማይለዩ ሁሉ በዚያ መልክ በታላቋ ደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም በስተቀኝ ጠባቢት በተባለ ቦታ የቅዱስ ሚካኤል ታቦት ሲተከል በደብረ ወርቅ ማርያም በስተግራ በሚገኘው ጀር በሚባለው ተራራ ላይ የቅዱስ ገብርኤል ታቦት ተተክሎ ይኖር ነበር ።

ከብዙ ዓመታት በኋላ ግን በዘመነ መሳፍንት ቀራንዮ ልብ ጋሻ እየተባለ ከሚጠራው ዋሻ በተነሣው ሰደድ እሳት ቤተ ክርስቲያኑ በመቃጠሉ አሁን እንደገና እስከተቋቋመበት ጊዜ ድረስ ጠፍ ሁኖ ቆይቷል በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በአደረባቸው ሰዎች አማካይነት የዚህ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ቦታው በአዲስ መልክ በተመሠረተ ጊዜ የሚአስገርም ዋሻና በውስጡም ብዙ አጽመ ቅዱሳን ተገኝቶበታል ሌላው የሚአስገርመው ነገር ደግሞ ለዚህ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውለው በአካባቢው የሚገኘው ጥቁር ደንጋያ ከአንድ ሜትር ተኩል በላይ ርዝመት ያለው ሲሆን መልካም ባለሙያ አሳምሮ ከጠረበው ደንጋይ ይልቅ የተስተካከለና ያማረ ነው ።

ዕፁብ ድንቅ የሆኑ ታአምራት ዛሬ የሚፈጸምበት የጀር ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ለብዙ መቶ ዓመታት ጠፍ ሁኖ ሲኖር አሁን በአዲስ መልክ ሊመሠረት የቻለው ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ እጅ እግሩ ሽባ ሁኖ የሚኖር አንድ አሳዛኝ በሽተኛ በአየው ራዕይ ነበር ይህ እጅ እግሩ ተጣጥፎ የተወለደ በሽተኛ በቤተ ሰቦቹ ርዳታ ከቤት አዳሪ እየተነሣ እየወደቀ ሲኖር አንድ ቀን በሕልሙ ሊቀ መላእክት ቅ/ገብርኤል ተገልጾ አሁን ጸበሉ ከፈለቀበት ቦታ ላይ በግልጽ በማሳየት ወደዚያ እንዲሄድና በዚያ በሚገኘው ውሃ ቢታጠብ እንደሚያድነው ይነግረዋል ።

ያም በሽተኛ ከዕንቅልፉ እንደነቃ ዘመዶቹ በራዕይ ወደ አየው ቦታ እንዲወስዱት ይጠይቃቸዋል እ ነ ር ሱ ም ከ ቤ ት ወ ጥ ተ ህ የ ማ ታ ወ ቅ እ ን ዴ ት የ ተ ለ የ ቦ ታ ታ ው ቃ ለ ህ እ ያ ሉ ሊወስዱት ስላልቻሉ በግድ ስለአለቀሰባቸው ወደ ተባለው ቦታ አዝለው ይወስዱታል ከዚያ ተአምራት ከሚሠራበት ቦታ ሲያደርሱት በሕልሙ ያየውን በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ እዚህ አውርዱኝ ይላቸዋል ከዚያ ሲያወርዱት በዘንዶ መሰል አውሬ እየተጠበቀ ያገኙዋል አውሬውም ቦታውን ሊለቅለት ባለመቻሉ አዝኖ ሲመለስ አሁንም በሕልሙ ለዚህ ዘንዶ መሰል አውሬ በቅ/ገብርኤል ስም መክፈልት (ጸዲቅ) ቢጤ ቢሰጠው እንደሚለቅለት ይነግረዋል ። እርሱም በራዕይ በተነገረው መሠረት የተባለውን ሲጥልለት ቦታውን ይለቅለታል ።

ከዚያ ላይ በተገኘው ጸበል ሲጠመቅ ወዲያውኑ በሚአስገርም ሁኔታ ከደዌው ይፈወሳል መሬት ለመሬት እንኳ በራሱ ኃይል መላወስ የማይችል ታዝሎ የሄደ በሽተኛ ቆሞ እየተጓዘ ወደ ቤቱ ተመለሰ ያ መሬት ለመሬት እንደልቡ መንቀሳቀስ የማይችል በሽተኛ በአሁኑ ጊዜ ከቡዳ መዝራዕት ኀልማሳ ሁኖ የጦር መሣሪያውን ታጥቆ የአዲሱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ዘበኛ ሁኖ በማገልገል ላይ ነው ።

ከዚህም ሌላ ብዙ ከአልጋ ላይ መንቀሳቀስ የማይችሉ በሽተኞች ፀበሉ እቤታቸው ድረስ እየሄደላቸው ሲጠጡት የተፈወሱት ሕሙማን ብዙ ናቸው እንዲሁም በልዩ ልዩ የመጤ እምነት ተበክለው ደዌ አድሮባቸው ጸበሉን ጠጥተው በመዳናቸው ወደ እውነተኛይቱ ኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው የተመለሱት አያሌ ናቸው ። የዚህ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ መልክ በሚሠራበት ረጅም ተራራ ላይ ሐምሌ ፲፱ቀንና ታኅሣሥ ፲፱ ቀን በየዓመቱ የቅ/ገብርኤል በዓል ዕለት የብርሃን ዓምድ ተተክሎ

www.ethiopianorthodox.org

ከሌሊቱ ፩ ሰዓት እስከ ሌሊቱ ፲ ሰአት ድረስ ሲያበራ መላው ሕዝበ ክርስቲያን ይመለከተዋል ። ሌላው ደግሞ የሚአስገርመው በዚሁ ተአምረኛ ታቦት ስም በፈለቀው ፀበል ላይ ሕዝቡ ተሰብስቦ በጸበሉ በመጠመቅ ላይ እንዳለ ከወደምሥራቅ የመጣ እንደጀት ያለ ነገር ከኋላው የእሳት ብልጭልጭታ ያለው በብርሃን የተሸፈነ በጸበሉ ላይ ሲያንጃብብ ቆይቶ ከእዚያው እንጸባራቂው አካል ቀስተ ደመና ወጥቶ በጸበሉ ላይ ዐርፎ ከቆየ በኋላ ወደሰማይ ተመልሷል እንግዲህ በአጠቃላይ በዚህ አስገራሚ ጸበል የሚፈጸሙትን ልዩ ልዩ አስደናቂ ተአምራት በጽሑፍ ለመግለጽ የሚቻል አይደለም የእግዚአብሔር ጸጋ ያደረበት በጎ ክርስቲያን ሁሉ ወደዚያው ሂዶ በዐይን ዐይቶ በረከት ተቀብሎ ቢመለስ መልካም መሆኑን ሳላስታውስ አላልፍም ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# ቅዱስ ገብርኤል ሌባውን ያዘ

በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ ፣ ፲፬ ቀበሌ ፲፰ በሚገኘው መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ/ም ለስርቆት የገባ አንድ ሰው ያለገመድ እጅ እግሩ ታስሮ አንገቱን እንደቆለመመ ዐረፋ እየደፈቀ ከቤተ መቅደሱ በራፍ ሥር በዕንቅልፍ ሰመመን ወድቆ ተገኝቷል ።

ታሪኩ እንዲህ ነው በየዓመቱ በዐቢይ ጾም ሰሞን ቅዳሜ ቅዳሜ የጾመ ኢየሱስ ዋዜማ ስለሚቆም ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ/ም ቅዳሜ ከቀኑ በ፱ ሰዓት የተለመደው ደወል ተደውሎ ዲያቆኑ የቤተ ክርስቲያኑን በር ከፍቶ በሚገባበት ጊዜ ሌባው ከቤተ መቅደሱ በራፍ ላይ በእንቅልፍ ሰመመን ወድቆ ያየዋል ።

ወዲያው ለአካባቢው ቀበሌና ፖሊስ ጣቢያ ለዜና አገልግሎት መምሪያ ጉዳዩ ተነግሮ የሚመለከታቸው ሰዎች እስከሚመጡ ድረስ ካህናቱና ምእመናኑ የቅዱስ ገብርኤልን ገቢረ ተአምራት በርቀት ሁነው ሲመለከቱ ቆዩ ከፖሊስ ጣቢያና ከቴሌቪዥን አገልግሎት ፖሊሶችና ጋዜጠኞች ከመጡ በኋላ የስርቆት ሥራ ሲፈጽም በቅዱስ ገብርኤል ተአምራዊ ኃይል የታሰረው ሌባ በቴሌቪዥንና በፎቶግራፍ ከተቀረጸ በኋላ ቀስቅሰውት የስርቆቱን ሁኔታ በዝርዝር ሲናገር ሰው ሁሉ ለማስቀደስወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ እኔም አብሬ ገባሁ ቅዳሴው ተፈጽሞ ሕዝቡ ሲወጣ በመጋረጃ ተሸፍኜ ተደብቄ ቀረሁ ከዚያም ተረኛው ዲያቆን መስኮቶቹንና በሮቹን ዘግቶ ሲወጣ እኔም በመጀመሪያ የሙዳየ ምጽዋቱን ሳጥን ፈልቅቄ ብርና ሳንቲሞችን በነጠላየ ላይ ዘረገፍኩ ብሮቹና ሳንቲሞቹ እንደጠበቅሁአቸው ሁነው አላገኘኋቸውም ።

ወደ ሌላ ክፍል አምርቼ አንድ ጃንጥላ አገኘሁ ከዚያም ምርጥ ምርጥ ዕቃ ያለበትን ስለላየን በመቀጠል ስመለከት በአንደኛው ክፍል ስደርስ ትልቅ የግድግዳ ሰዓት አገኘሁ በወንበር ተንጠላጥየ አወረድሁት እነዚህን በአንድ ቦታ አዘጋጅቼወደውስጠኛው ክፍል ስገባ ማለት የቤተ መቅደሱን በር ልፈለቅቅ ስል ዕንቅልፍ እንቅልፍ አለኝ ወዲያውም እግሬና ወገቤ እጄ በሰንሰለት የታሰረ ይመስለኛል ወደቅሁ ከዚያ በኋላ የሆነውን ሁሉ አላውቅም ማንነቴን ያወቅሁት አሁን እናንተ መጥታችሁ ስትቀሰቅሱኝ ነው ብሏል ።

ይህን የስርቆት መጥፎ ሥራ ለመፈጸም እንዴት እንደተገፋፋ ተጠይቆ ሲመልስ አንዲት ሴት ሙዳየ ምጽዋት ውስጥ ብር ጠቅልላ ስታስገባ በማየቴና እኔም ችግረኛ ስለሆንኩ ጠቀም ያለ ገንዘብ አግኝቼ ወደ ሀገሬ ለመመለስ ነበር በማለት ተናግሮአል ። በስርቆት በእጅ ላይ የተገኙ ።

፩ኛ ከሙዳየ ምጽዋት ሣጥን ሰብሮ በጨርቅ የጠቀለለው ፳፬ ብር
፪ኛ ከቅኔ ማኅሌት የተሰቀለ አንድ ትልቅ የግድግዳ ሰዓት ።
፫ኛ ቀድሞ የንግሥት ጸሎት ማድረሻ እየተባለ የሚጠራውን ክፍል ቁልፉን ሰብሮ በመግባት ለዕለት ማገልገያ ከተቀመጡት ጃንጥላዎች ውስጥ አንድ ጃንጥላና አንድ መስቀል በማያዝ ከወጣ በኋላ ይህም አልበቃ ብሎት ወደ ቤተ መቅደሱ በራፍ በመጠጋት በሩን ለመስበር ሲታገል ሕሊናውን ስቶ በመውደቅ እጅ እግሩ በመልአኩ ኃይል ተሳስሮ ሊያዝ ችሏል ። ሌባው አሠራረቁን በዚህ ሁኔታ ተናግሮ እንደጨረሰ ለዚሁ ጉዳይ ከፖሊስ ጣቢያ በመጡት አባላት ተወስዶ በምርመራ ላይ ነበር ሲል የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል አስተዳደር በጊዜው ገልጧል ። በነገራችን ላይ ሌባው ጉደታ ይባላል ።

የቅዱስ ገብርኤል ኃይለ ተአምር በየጊዜው የሚፈጸም ቢሆንም ይህ አስገራሚ ነገር ማለትም ብዙውን ነገር ሲአጠፋ ታግሦ ቆይቶ የቤተ መቅደሱን በር ለመስበር ሲታገል ሕሊናውን አስቶ እጅ እግሩን ያለሰንሰለት በኃይሉ ጠፍሮ አስሮ ለሚይዙት ማስረከቡ በእጅጉ የሚአስገርም ነገር ስለሆነ ምእመናን እንዲያውቁትና የቅዱስ ገብርኤልን ኃይለ ተአምራት እንዲረዱት ቀርቦአል ።

www.ethiopianorthodox.org